# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 71 መስከረም 14 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

> በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት የሚቻለው የሥርዓቱን ግፈኛ ገጽታ ለመሸፈን ወያኔ በሚጠራው ምርጫ አይደለም፡፡

## ወያኔ በመጪው ወር የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን እንደሚያስረክብ ታወቀ

ኢትዮጵያን በማፈራረስ ታሪኩ የሚታወቀው አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ፣ በሚቀጥለው ወር እጅግ ሰፊ የሆነውን የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ሱዳን ትሪቢዩን የተባለው ድህረገጽ የሱዳንን ባለስልጣነት ጠቅሶ ዘግቧል።

የከሀዲው መለስ ዜናዊ ቡድን፣ አባቶቻችን ለዘመናት በደምና በአጥንታቸው ያቆዩትን መሬት በመሸንሸን ለሱዳን መስጠት የፈለገው፣ የካርቱም መንግስት የወያኔ ተቃዋሚዎችን በአገሩ እንዳያደራጅ ለማድረግ መሆኑን በሱዳን አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተናግረዋል።

በገዳሪፍ አካባቢ የሚኖረው ሰለሞን ሹምየ የተባለው ነጋዴ ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገረው፣ የሱዳን መንግስት ከኢትዮጵያ ባገኘው መሬት ደስተኛ በመሆኑ፣ በመልሱ ወያኔን ይቃወማሉ ያላቸውን ሀይሎች ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ እየተዘጋጀ መሆኑን ሱዳኖች ይነግሩናል ብሏል።

“መለስ ዜናዊ ለስልጣኑ ሲል የአገሪቱን መሬት እየቆረሰ መስጠቱ የታወቀ ነው” የሚለው የመተማ ነዋሪው አበበ አጎናፍር በበኩሉ “ሱዳኖች እድሜ ለአንድ ባንዳ ያለምንም ጦርነት ጅጎኖች አባቶቻችን ያቆዩትን መሬት ወሰዱ። የእኛ ትውልድ ያገሩን አንድነት ለማስጠበቅ ባለመቻሉ አፍራለሁ።” ብሏል።

ይህ ሁሉ ባለስልጣን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በውጭ አገር ሄዶ እንደሚታከም የታወቀ ሲሆን፣ ለአንድ ጊዜ ህክምናም መጓጓዣ፣ ሆቴልና ሌሎችንም ወጪዎች ጨምሮ ከ10 ሺ ዶላር በላይ ነው።

ለመከላከያ ሰራዊቱ ጥሪ ያቀረቡት ደግሞ በጎንደር ከተማ የታሪክ መምህር የሆኑት አቶ አገኘሁ አራጌ ናቸው። አቶ አገኘሁ እንደሚሉት አባቶቻችን ለዘመናት ተዋድቀው **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## ወያኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ የጀመረውን ጥቃት አጠናክሮ ቀጥሎበታል ተባለ

ላለፉት 19 አመታት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤ/ክ ለማዳከም ውስጥ ለውስጥ ስራውን ሲሰራ የቆየው የወያኔ አገዛዝ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እየወሰደ ያለውን እርምጃ በአደባባይ ማስነገር መጀመሩን የወያኔ የመገናኛ ብዙሀን ዘገባዎች እያመለከቱ ነው።

ከትናትን በስቲያ የወያኔው ቴሊቪዥን ባሰራጨው ዜና ላይ፣ አገዛዙ በማህበረቅዱሳን አባላት ላይ እርምጃ እንደሚወስድ አስጠንቅቋል።

የማህበረ ቅዱሳን አባላት “በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ የዘረኝነት አሰራር ተስፋፍቷል፣ ጥቂት ግለሰቦች የቤተክርስያኗን ሀብት እየዘረፉ ባለጸጋዎች ሆነዋል፣ ቤተክርስቲያኑዋ ባለባት የአስተዳደር መበላሸት የተነሳ ሀይማኖታዊ ተግባሯን ልትወጣ አልቻለችም፣ በእምነት አባቶች ላይ ድብደባና ማስፈራሪያ እየደረሰነ ነው ወዘተ” የሚሉ የመብት ጥያቄዎችን ማቅረባቸው ታውቋል። አባ ጳውሎስ ግን ቅዱስ ሲኖዶሱን ሳያማክሩ የወያኔ ባለስልጣናትን በጎን በማስመጣትና የማህበረ ቅዱሳን አባለት በፖለቲካ ጣልቃ እየገቡ ነው የሚል ክስ በማቅረብ ለአባላቱ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው ማድረጋቸው ታውቋል።

የወያኔ አባላት ስለሚወስዱት እርምጃ ይፋ ባያደርጉም የውስጥ ምንጮቻችን እንደገለጹልን ከሆነ ግን በርካታ ወጣት የማህበረ ቅዱሳን መምህራን ወደ ወህኒ ሊወርዱ ወይም ድብደባና ግድያ ሊፈጸምባቸው ይችላል ተብሎአል።

እንደ መከላከያ፣ፓሊስና የደህንነት መስሪያቤቶች ሁሉ የኦርቶዶክስ ቤ/ክም የምትሽከረከረው በትግራይ ሰዎች ሲሆን፣ እነዚህ የትግራይ ሰዎች በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ከቤተክርስቲያኗ ካዝና በመውሰድ ኢንቨስተር መሆናቸውን መረጃዎችን ዋቢ አድርገው ምንጮቻችን ዘግበዋል። በአሁኑ ጊዜ አሉ የሚባሉ ሚሊየነር የትግራይ ነጋዴዎች በአንድ በኩል ከወያኔ ገዥዎችና የንግድ ተቋማት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና ከአንዳንድ የማህበራዊ ተቋማት ጋር የጠበቀ ትስስር በመዘርጋት የአገሪቱን ሀብት ሙሉ በሙሉ በእጃቸው እያስገቡ ሲሆን፣ በርካታ ቤተክርስቲያኖች ግን የስራ መስኪያጃ ገንዘብ አጥሯቸው ሀይማኖታዊ ስራዎችን ለመስራት መቸገራቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## ኦፌዴንና ኦህኮ በራካታ አባሎቻቸው መታሰራቸውን ገለጹ፣ በመጪው ምርጫ ለመሰታፍ እንደሚቸገሩም ገለጹ

የኦሮሞ ፌደራሊስት ዲሞክራሲ ንቅናቄና የኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ ባለፈው ዓርብ መሰከረም 8 ቀን 2002 ዓም በጋራ ባወጡት መግለጫ ዜረኛው የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ ከ412 በላይ አባሎቻቸውን እንዳሰረባቸው ገልጸዋል። በአባሎቻቸው ላይ የሚደርሰው ማስፈራሪያና እንግልት ከጳጉሜ 2001 አም ጀምሮ በከፋ ሁኔታ መቀጠሉን የሚናገረው የሁለቱ ፓርቲዎቹ መግለጫ፣ በምርጫ 97 ወቅት አሸንፈው በክልልና በፌዴራል ፓርላማ ምክር ቤቶች ውስጥ እየተሳተፉ ያሉት አባላቶቹ ጭምር በህገመንግሥቱ ያላቸው ይለመታሰር መብት በህግ ሳይገፈፍ በወያኔ ካድሬዎችና ፖሊስ በተለያዩ ጊዜያቶች ለእስር እና መሰል እንግልቶች እንደተዳረጉበት በዋቢነት ጠቅሶ፣ ተራ አባላቱና ደጋፊዎቹን ሆን ብሎ ለመቅጣት አገዛዙ በወሰደው አርምጃ ላለፉት 4 አመታት በመንግሥት ከሚቀርቡት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዳይሆን ከፍተኛ አድልዎ እየተፈጸመባቸው እንደሆነ አጋልጠዋል:: መግለጫው አያይዞም በአሁኑ ጊዜ የሚታየው አፈናና አስራት በአስቸኳይ ካልቆመ በቀር በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል በማለት አስጠንቅቆ ; የወያኔ አገዛዝ በእስር ላይ የሚገኙ አባሎቹን ሁሉ አሁኑኑ እንዲፈታና በካድሬዎችና በፖሊስ ሃይል እየተፈጸመ ያለው ህገ መንግስትን የሚጥስ እርምጃ እንዲገታ፣ የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚዎች እንዲያከብሩት በተደጋጋሚ የሚለፍፈውን የራሱን ህገመንግሥት እንዲያከብር ጠይቋል።

የ8ኛና የ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ያለፉ ተማሪዎች የአህዴድን የአባልነት መታወቂያ ወረቀት ካላመጡ በትምህርት ቤት እንዳይመዘገቡ እየተደረገ ነው ያለው የሁለቱ ፓርቲዎች መግለጫ አባላቶቹን አስገድዶ ፎቶግራፍ ማንሳትና ላልታወቀ አላማ የጣት አሻራቸውን መውሰድ የተለመደ የመብት ጥሰት ሆኖአል ብሎአል::

ባለፈው ሁለት ሳምንታት ውስጥ በሁለቱ ፓርቲዎች አባላት ላይ ለየት ያለ የጅምላ እስራት ዘመቻ የተከፈተው የሁለቱም ፓርቲዎች መሪዎች መድረክበመባል በሚታወቀውና በቅርቡ በተቋቋመው የተቃዋሚዎች ስብስብ ውስጥ ጎላ ብለው እየታዩ በመምጣታቸው የወያኔን መሪዎች ስላሳሰበ ከወዲሁ ፓርቲዎቹን ለማዳከም እንደሆነ አንዳንድ የፖለቲካ አዋቂዎች ይናገራሉ :: ለወያኔ መሪዎች ቅርበት ያላቸው የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መረጃ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ንቅናቄ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በህገመንግስቱ አንቀጽ 39 ላይ የሰፈረውን የመገንጠል መብት በአደባባይ በመቃወማቸውና በቅርቡ ለቪኦኤ የአማሪኛው ክፍል በሰጡት ቃለመጠይቅ አንቀጽ 39ን ማን ለምን በህገመንግሥቱ ውስጥ እንዲካተት እንዳደረገ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል ማለታቸው እነ በረከት ስምኦንን እጅግ እንዳስቆጣ የሰሞኑ ጥቃትም የዚያ አቋም አጻፋ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል:: ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑን ዕድሜ ርዝመት የሚያሰላው በህዝቦች መካከል **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## የኢድአል ፈጥር በመላው አለም ተከበረ፣ ግንቦት 7ትም መልካም ምኞቱን ገልጿል

የ1430ኛውን የኢድ አል ፈጥርን በአል ምክንያት በማድረግ ግንቦት 7 ባለፈው ቅዳሜ በላከው የመልካም ምኞት መግለጫ ላይ እንደገለጸው፣ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ይህን ታላቅ በአል ሲያከብር ሊከፋፍሉትና ሊያጋጩት የሚሞክሩትን ሀይሎችንም አጥብቆ ሊዋጋ ይገባል ብሏል።

ንቅናቄው እንደሚለው የወያኔ አገዛዝ ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረውን የኢትዮጵያን ህዝብ በሀይማኖት በመከፋፋል በማጋጨት የስልጣን እድሜውን ለማራዘም የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ሙስሊሙ ማህበረሰብ አጥብቆ ማውገዝ ይጠበቅበታል።

ወያኔ አንዴ የሙስሊሞች ጠበቃ በመሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ የእስልምና አክራሪነት አገራችንን ሊወራት ነው የሚል የማደናገሪያ ወሬ በማስወራት ህብረተሰቡን ከፋፍሎና አዳክሞ ለመግዛት የሚያደርገው ጥረት እየታወቀበት መምጣቱን ግንቦት 7 ገልጾ፣ በቅርቡ የደሴ ከተማ ሙስሊሞች የወያኔን ድብቅ ተንኮል ለማጋለጥ የተጓዙበትን እርምጃም አድንቋል።

ኢትዮጵያን የሁሉም ሀይማኖት ተከታዮች ተቻችለው በእኩልነት የሚኖርባት አገር ለማድረግ ግንቦት 7 ሌት ተቀን እየሰራ መሆኑን ገልጾ፣ ሙሲሊሙ ማህበረሰብም ለዚህ አላማ እውን መሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጠይቋል።

## ለነፃነት የሚደረገውን ትግል ማገዝ የመኖሪያ ቦታ የማይወስነው የሞራልና የዜግነት ግዴታ ነው

የንቅናቄያችን ሊቀመንበር የአዲስ ዓመት መልእክት ያተኮረው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት አባላትና ደጋፊዎቻችን ለትግላችን መፋፋም ማድረግ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ነበር። ዋነኛው የትግል ሜዳችን ኢትዮጵያ መሆኗ እና ለወያኔ አፈና ያልተጋለጠ የአደረጃጀት ስልትን በሚገባ ማስተዋወቅ ይገባ ስለነበር ለአገር ውስጥ እንቅስቃሴዓችን ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ነበር። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ድርጅታዊ አቅም ማጎልበት ዋነኛ ትኩረታችን ቢሆንም በውጭ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎም ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጠው ጉዳይ ነው።

እያንዳንዱ ፍትህና ነፃነትን ናፋቂ የሆነ ዜጋ ሁሉ ወያኔን በኢትዮጵያ የመጨረሻው አምባገነን ለማድረግ በሚደረገው ትግል ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ አለ። ከሁሉ አስቀድሞ ግን በተለይም በተማረውና ከሥልጣኔ ጋር ቀረቤታ ባለው ወገናችን ዘንድ የሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አጽንዖት ሊሰጣቸው ይገባል።

1. ለፍትህ መስፈን ዋጋ መከፈል አለበት። ነፃነትም ውድ ናት፤ ህይወትን ሳይቀር ታስከፍላለች። ሆኖም ፍትህ አንዴ ከሰፈነ ዋጋ የከፈለውም ያልከፈለውም እኩል ተጠቃሚ ይሆናል። ነፃነትም አንዴ ከተረጋገጠ አርበኛውም ባንዳውም እኩል ይጠቀማሉ። በዚህም ምክንያት ብልጥ ነን ባዮች ሌሎች ታግለውላቸው ፍትህና ነፃነትን እስኪያሰፍኑላቸው አድፍጠው ይቆያሉ። ጥቂቶች በሙሉ አቅማቸው ሲታገሉ እነሱ ስለፍትህና ነፃነት ዲስኩር እያሰሙ በጎን ጊዜዓዊ ጥቅሞችን ይለቃቅማሉ። በጥቂቶች አቅም ለውጥ ስለማይመጣ ነጻነት ናፋቂዎችን ጨምሮ ሁሉም ፍትህና ነፃነትን እንደናፈቁ በባርነት ተቀጥቅጠው እንዲገዙ በቀጥታና በተዘዋዋሪ አስተዋጽ'ኦ ያደርጋሉ ። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት የሚገኙ በተለይም ዘመናዊውን ትምህርት የቀመሱ ዜጎች ሊወስዱት የሚገባው የመጀመሪያው እርምጃ ይህንን ሥር የሰደደውን ብልጣ ብልጥ አድርባይነትን መዋጋት ነው። ይህ ሥር የሰደደ አድርባይነት ነው ደካማው ወያኔ ኢትዮጵያን ቀጥቅጦ ለሃያ ዓመታት መግዛት ያስቻለው። አሁን ወሳኝ ፍልሚያ ውስጥ ነን። ፍትህና ነፃነት ይገባናል የምንል ከሆነ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ እንሁን።
2. እርግጥ ነው ፍትህና ነፃነት ውድ ዋጋ ያስከፍላሉ፤ ግን እዳውን ከተካፈልነው የእያንዳንዳችን ድርሻ ትንሽ ነው። ስለዚህም የፍትህና ነፃነት ውድነት ሊያስበረግገን አይገባም። ሁላችንም በአንድ ልብ ከተነሳን ወያኔን ለማስወገድና የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት ከእያንዳንዳችን የሚፈለግብን ጥረት ትንሽ እንደሆነ ማወቅ ጠቃሚ ነው። ወያኔ ማኅበራዊ መሰረት የሌለው ደካማ ሥርዓት ነው። የእያንዳንዳችን ትናንሽ ጥረቶች ሲቀናጁ ወያኔን ለማስወገድ ከሚያስፈልገን በላይ ኃይል ይፈጥራሉ። ሃምሳ ሎሚ ላምሳ ሰው ጌጡ፤ ላንድ ሰው ግን ሸክሙ ነው እንዲሉ ወያኔዎችን የማስወገድ ኃላፊነት ወደ ጥቂቶች ትከሻ ከወረወርን ግን ነፃነታችንን አሳልፈን መስጠታችንን እንወቅ፤ ከተጋገዝን ግን በእያንዳንዳችን ላይ የሚደርሰው ድርሻ ኢምንት ነው።
3. ለዘላቂ ጥቅም ሲባል ጊዜዓዊ ምቾቶችን መሰዋት ባህል ማድረግ ይኖርብናል። ዛሬ ከወያኔ ጋር በመሞዳሞድ የሚገኝ ጥቅም በልጆችና በልጅ ልጆች ህይወት፤ በአጠቃላይ በወደፊት ትውልድ ላይ ከሚያመጣው መከራ ጋር መመዘን ይኖርበታል። የእለት ተእለት ተግባሮቻችን የወደፊቱን ትውልድ እጣ ፈንታ እሳቤ ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል። ቀድሞ ያልተሰሩ ነገሮች እኛን ለወያኔ ዳርጎናል። ከዚህ ትምህርት ወስደን ወያኔን ያህል እዳ ለልጆቻችን ማሳለፍ ቀርቶ እስካሁን ማቆየታችንም ሊቆጨን ይገባል።

ከእነዚህ መሰረታዊ የመልካም ዜጋ ግዴታዎች በመነሳት በውጭ አገራት የምትገኙ ኢትዮጵያዊያትና ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ መንገዶች ትግሉን ልታግዙ ትችላላችሁ፤ ይገባልም። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥቂት ጠቋሚ ምሳሌዎች ብቻ ናቸው።

1. የተደራጀ ትግል ባነሰ ወጪና በአጭር ጊዜ ውጤታማ ያደርጋልና ንቅናቄያችንን ይቀላቀሉ። ለአባሎቻችን የሚመቹ የአደረጃጀት መዋቅሮችን፣ የትግል ስልቶችን እና የተሳትፎ ዓይነቶችን አዘጋጅተናል። አቅም በፈቀደ መጠን ድርጅታችንን ለማዘመን ጥረት እናደርጋለን። ስለሆነም እኛን መቀላቀል ለትግሉ አስተዋፅዖ ከማድረግ በተጨማሪ ለዘመናዊ አስተሳሰብና ቴክኖሎጂ ቅርብ ያደርጎታል።
2. በማናቸውም ምክንያት ከኛ የሚመርጡት ፀረ_ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ካለ ይቀላቀሉት።
3. ግንቦት 7ን እና/ወይም ሌሎች ፀረ_ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶችን በገንዘብዎ፣ በእውቀትዎና በጊዜዎ ይርዱ።
4. የህሊና እስረኞችን ይዘክሩ፤ ቤተሰቦቻቸውን ይደግፉ።
5. የዲፕሎማሲው ትግል አካል ይሁኑ። ሰላማዊ ሰልፍ ይውጡ፤ በረሃብ አድማዎች ይሳተፉ።
6. ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የወያኔዎችን እኩይ ተግባራት ከማጋለጥ አይቦዝኑ። ለፖለቲከኞች፣ ለሕዝብ ተወካዮች፣ ለሥራ ባልደረቦችዎ፣ ለክፍል ጓደኞችዎ ዜግነትን ሳይመርጡ የወያኔን ዘረኝነት፣ ጨፍጫፊነት : ዘራፊነትና አምባገነንነት ያሳውቁ።
7. በማናቸውም መንገድ ወያኔን የሚጠቅም ተግባር አይፈጽሙ። የኢንቬስትመንት ግብዣውን አይቀበሉ። በመሬት፣ በመብራት ኃይል ቦንድ፣ በአካባቢ ልማት ወዘተ አይደለሉ።
8. ለቤተሰቦችዎ ገንዘብ ሲልኩ የወያኔ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ማስታገሻ በማይሆን መንገድ ያድርጉት። ኦፊሲያላዊ መንገዶችንም ሆነ ወያኔ በየአገሩ ያደራጃቸው የገንዘብ ማስተላለፊያዎችን አይጠቀሙ።
9. ከወያኔ ድርጅቶች ጋር ፈጽሞ አይነግዱ። እቃዎቻቸውን አይግዙ፤ አገልግሎቶቻቸውን አይጠቀሙ።
10. አገር ቤት ለሚገኙ ዘመዶችዎ የአማራጭ መረጃዎች ምንጭ ይሁኑ። የሰሙትንና የአነበቡትን ያካፍሏቸው።
11. ወያኔ እየሸረበልን ባለ የዘርና የሃይማኖት ቅራኔ ውስጥ እንዳንገባ፤ በኢትዮጵያዊያን መካከል መግባባት እንዲሰፍን ተግተው ይስሩ። በኢትዮጵያዊያን መካከል በዘርና ሃይማኖት ልዩነት ባለማድረግ አርዓያ ይሁኑ።
12. ከአሉባልታ ነፅተው የተግባር ሰው ይሁኑ። ፓለቲካችንን ከውሸት፣ ከጭፍን ጥላቻ እና ተራ ወሬዎች ለማንፃት ተግተው ይስሩ።
13. ጠዋት "ዛሬ ለትግሉ የማበረክተው ምንድነው?" ብለው ይጠይቁ፤ ማታ ጠዋት ያሉዋቸውን ፈጽመው እንደሆነ ራስዎን ይፈትሹ።

ፈጣን ውጤት የምናገኘው በርትተን ስንሰራ ብቻ መሆኑን ፈጽሞ አይዘንጉ። ከላይ የተዘረዘሩትን ከከወንን ወያኔን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የምንመኛት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መሰረት በአለት ላይ እንገነባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ኦፌዴንና ኦህኮ በራካታ አባሎቻቸው . . . ከገጽ 1 የዞረ

ተፈጥሮአል ብሎ በሚያስባቸው መከፋፈልና የእርስ በርስ መጠራጠር እንደሆነ ይታወቃል ያሉት ምንጫችን በተለይ በኦሮሞው ህዝብና በሌሎች መካከል ያለው ወያኔ የፈጠራቸው ስጋቶችና ጥርጣሬ እየተወገደ መምጣት ለአገዛዙ ከፍተኛ የራስ ምታት ሆኖበታል ብለዋል።

በምርጫ 97 ወያኔ የፈቀደላቸውን የምክር ቤት መቀመጫ ተቀብለው ፓርላማ ከገቡት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዋንኞቹ የሆኑት ኦፌዴንና ኦህኮ በተከታታይ ላላፉት 4 አመታት በፓርላማ ውይይት ወቅት ስለ አባላቶቻቸው በግፍ መታሰር: መገደልና ከአገር መሰደድ አቤቱታቸውን ሲያሰሙ ኖረዋል ። ከጊዜ ወደጊዜ  በአባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ላይ እየተጠናከረ የመጣው ጥቃት ተስፋ እንዳስቆረጣቸው በተለያዩ መድረኮች ጭምር የሚናገሩት የሁለቱም ፓርቲ መሪዎች  ወያኔ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት ለማግኘት ሲል ብቻ በዚህ አመት ሊያደርግ በተዘጋጀው ምርጫ ተብዬ ተውነት ተጠናክረው እንዳይፋለሙት ለመከላከል እየተወሰደ ያለ እርምጃ መሆኑን አድስ አበባ ለሚገኙ ም'ዕራባዊያን እርዳታ ለጋሾች ማሳወቃቸው ታውቆአል።

ከግንቦት 1997 ምርጫ በሁዋላ ወያኔ በተቃዋሚ መሪዎችና ደጋፊዎች ላይ የሚወስደው የአፈና እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠሉን የተለያዩ ዘገባዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥም ስለዲሞክረሲያዊና ፍትሀዊ ምርጫ ማውራት ፈጽሞ እንደማይቻል ብዙዎች ይስማማሉ።

## ወያኔ በመጪው ወር የኢትዮጵያን መሬት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ያስጠበቁትን ድንበር ያሁኑ የመከላከያ ሰራዊት በተራው የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት። ሰራዊቱ በማይመለከተው አገር እየሄደ ይሞታል። በሚመለከተው ጉዳይ ግን እጁን አጣጥፎ ይመለከታል። ታዲያ መከላከያ ሰራዊቱ የአገሩን ዳር ድንበር ካላስጠበቀ የማንን ጓሮ ሊጠብቅ ነው " ሲሉ በቁጭት ተናግረዋል።

ሰራዊቱ የመለስን የባንዳ ስራ መቃወም አለበት የሚሉት አቶ አገኘሁ፣ ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን ህዝቡ ሆ ብሎ ተነስቶ ድንበሩን ማስጠበቅ እንዳለበት አሳስበዋል።

የሱዳን መንግሰት በጥቅምት ወር ከወያኔ እጅ የሚረከበው መሬት ዘላቂነት እንደሌለው የሚናገሩ የህግ ባለሙያዎችም አሉ። አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የህግ ባለሙያ ሲናገሩ፣ "የወያኔ አገዛዝ ያገሪቱን መሬት ለሌላ አገር አሳልፎ ለመስጠት ህጋዊ ስልጣን የለውም ምክንያቱም አገዛዙ ከመጀመሪያውም የህዝብ ይሁንታ የሌለው ነው" ብለዋል። "የህዝብ ይሁንታ ያለው መንግሰት  በህጋዊ መንገድ በምርጫ ይመረጣል፣ የወያኔ አገዛዝ ግን  በስልጣን ላይ ያለው በጉልበቱ ነው" የሚሉት የህግ ባለሙያው፣ "አንድ  ህግ ህዝባዊም ሆነ አለማቀፋዊ  ተቀባይነት የሚኖረው ህጉን የፈረሙት ወገኖች የህዝባቸውን ውክልና ሲያገኙ ብቻ ነው፣ በዚህ ረገድ ሲታይ ወያኔ ምንም አይነት የህዝብ ውክልና የለውም" ሲሉ ገልጸዋል።

የወያኔን ድብቅ ተንኮል በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ አርሶአደሮች በድፍረት ማጋለጣቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ግንቦት 7ትን ጨምሮ በርካታ ድርጅቶችም ሲያወግዙት መቆየታቸው ይታወሳል።


በግንቦት 7  የፍትህ  የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ  ዘርፍ  በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ ክፍል 1

## 1. መግቢያ

ወያኔ ምርጫ 2002ን በተመለከተ የመራጩንና የተወዳዳሪውን ገደብ፤ የሚያመቸውን ጊዜና የምርጫ ዳኛውን በዚያውም የምርጫውን ውጤት ነድፎ ጨርሷል ... እኛስ?

እንደሚታቀው አብዛኛዎቹ የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባላት በግንቦት 1997 ምርጫ ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ የንቅናቄውም ከፍተኛ አመራር እንዲሁም በ1997 ምርጫ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፈ ነው፤ ስለምርጫው በቂ እውቀት አለው፡፡ አመራሩ የምርጫ 97 ልምድን አበጥሮ መርምሯል፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ ምርምር በመነሳት አሁን አገራችን በምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ምርጫ የሚኖረውን ትርጉም በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ‹‹ምርጫ የሕዝብን ድመፅ ህገወጥ በሆነ መንገድ ቀምቶ በጠመንጃ ኃይል ዘረኛና ዘራፊ አገዛዙን የዘረጋውን አምባገነናዊ የወያኔ አገዛዝ ህጋዊ እውቅና መስጠትና ማጠናከር ይሆናል›› ብሏል፡፡ ‹‹በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት የሚቻለው የሥርዓቱን ግፈኛ ገጽታ ለመሸፈን ወያኔ በሚጠራው ምርጫ አይደለም፡፡ እንዲያውም በአገራችን እውነተኛ ምርጫ ማድረግ የሚቻለው ወያኔ ከሥልጣን ተወግዶ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ባቀፈ የዲሞክራሲ የሽግግር ሂደት ማለፍ ስትችል ብቻ መሆኑን›› ግንቦት ሰባት በማያሻማ ቋንቋ ገልጧል፡፡ ግንቦት 7 ይህንን አይነቱን የሽግግር ሂደት በአገራችን ለማስጀመር ዲሞክራሲያዊ ራዕይ አንግቦ፣ ማኛቸውንም የትግል ስልት በመጠቀም ከሕዝብና ለዴሞክራሲያ ሂደቱ መጀመር ቅድሚያ ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በመደጋገፍ መራራውን ትግል ጀምሯል፡፡ ያም ሆኖ የ2002 የወያኔ የምርጫ ቲያትር ጊዜ እየደረሰ ነው፡፡ ይህን ተንተርሶ የተጠበቁና የማይቀሩ የማደናገሪያ እርምጃዎቹን ወያኔ መውሰድ ጀምሯል፡፡ ሕዝቡና የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ እንዲሁም በሃገራችን ያሉት የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ አባላት ለዚህ የወያኔ እስክስታ የሚመልሱት መልስ ሕዝባዊ ውይይት ስለሚያስፈልገው የንቅናቄያችንን አቋም ለመግለጽ ይህንን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

## 2. ምን ዓይነት ምርጫ፡ ነፃ ወይስ የሴራ ምርጫ?

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማለቅ በኋላ በታዳጊው ዓለም ጎራ ያሉ ሁሉም ዓይነት መንግሥታት ምርጫን የሥልጣናቸው ሕጋዊና ሞራላዊ መሠረት ለማድረግ እየሞከሩ ነው። ይህ የምርጫ ሙከራ እንደተጀመረም በምርጫ ወደ ሥልጣን የወጡትን መንግሥታት ከዚህ በፊት ከነበሩት ፈላጭ ቆራጭ የነገሥታት፣ የወታደራዊና የአንድ ፓርቲ አገዛዞች ጋር በማነጻጸር የተሻሉ ጅምሮች ናቸው የሚሉ እምነቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው ነበር። ምናልባትም እነዚህ ምርጫዎች በሂደት ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሄጃ በር ይከፍቱ ይሆናል በሚል መላምት በደፈናው እንደ መሻሻል የታዩበት ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ከ 20 ዓመታት ልምድ በኋላ የታየው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ቀደም ተብሎ ተይዞ የነበረውን ተስፋ ያደበዘዘ ሆኗል፡፡ እርግጥ ነው ጥቂት ምርጫዎች እውነተኛ የሆነ የዴሞክራሲ ሂደትና ግንባታ በጥቂት ሃገሮች ላይ እንዲጀመር አስችለዋል፡፡ ብዙዎቹ ምርጫዎች ግን ከቀድሞው ባልተሻለ ሁኔታ የፖለቲካ ጭቆና፡ የኢኮኖሚ ገፈፋና የጥቂት አምባገነኖች ግፈኛ አገዛዝ የመከለያ ሽፋን ሆነው አርፈውታል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዓለማችን ውስጥ አራትና አምስት አመት እየጠበቁና አስመሳይ ምርጫቸውን እያካሄዱ የአንድ ፓርቲ ወይም የአንድ ግለሰብ አገዛዛቸውን በምርጫ ስም የህጋዊነትና የሞራል ልባስ ለማለበስ ሙከራ የሚያደርጉ አምባገኖነች ቁጥራቸው እየተበራከተ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች በሥራ ላይ እየዋለ ያለው በማጭበርበር ሴራ ላይ የተመሰረተ ምርጫ ውጤቱ በጥቂቶች የበላይነት በዘር የተደራጀ የፖለቲካ ሥርዓት ማጠናከር ሆኗል፡፡ ከአገሪቱ ሕዝብ 5 በመቶ የማይበልጠውን የትግራይ ህዝብ ‹‹በትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭነቴ እወክላለሁ›› የሚል ነገር ግን የእዚህ ውክልና እንዳለው ግን ምንም አይነት ዴሞክራሲያዊ ማረጋገጫ የሌለው ጠባብ ቡድን፣ ዘረኛ አገዛዙን በመላው አገሪቱ ህዝብ ላይ የሚጭንበት የማጭበርበሪያ ስልት ምርጫ ሆኗል፡፡

ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ዓይነት የምርጫ ልምዶች በመነሳት በአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲና የምርጫ ሂደት የሚከታቱሉና የሚመረምሩ ጋዜጠኞችና ተመራማሪዎች ምርጫን በሁለት ቦታ ከፍለው እንዲያዩ ተገደዋል።

በአንድ በኩል ምርጫ የፖለቲካ ቡድኖች ትርጉም ባለው መልክ ተወዳድረው የሕዝብ ውክልና እና ተጠያቂነት ያለው መንግሥት መመሥረቻ ሁኗል። በዚህም ሂደት አገራት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን እየገነቡና እያጠናከሩ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ዲሞክራሲ ባህልና አሰራር እንዲጎለብት፣ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ እሴቶች ከፍተኛ ክብር እንዲሰጥ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሃገሮች ውስጥ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ እድገት መሰላል፤ የሰላምና የመረጋገት ዋስትና፤ የማኅበራዊ ችግሮች ማቃለያ እና የሰብአዊ ክብርና መብት ማስጠበቂያ መሣሪያ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ አምባገነኖች ምርጫን የሚፈልጉት ሥልጣናቸውን ሞራላዊና ህጋዊ ለማድረግ ብቻ እንደሆነ ግልጽ ሆኗል፡፡ እነዚህ አምባገነኖች በአንድ በኩል የመንግስት ሥልጣን መያዝ ያለበት በሕዝብ ነጻ ፈቃድ ላይ በተመሠረተ ምርጫ ነው የሚለው እሳቤ፣ የዘመኑ የሰው ልጆች ሁሉ ገዢ እምነት መሆኑን ተረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገንዘቡና ጉልበቱ ያላቸው በርካታ የዓለም አገሮች ለዴሞክራሲና ለምርጫ ትልቅ ቦታ እየሰጡ መምጣቸው ገብቷቸዋል፡፡ ይህ እውነታ አምባገነኖች እንደቀድሞው ‹‹የምን ምርጫ! የምን ዴሞክራሲ!›› ብለው እየደነፉ መቀጠል የማይችሉበትን ሁኔታ እንደፈጠረ ያውቃሉ፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ድሃና የመንግሥታዊ በጀታቸው ከፍተኛ መጠን ያለው ድርሻ በምዕራብ መንግሥታት እርጥባን የሚሟሉላቸው፤ የራሳቸው ኢኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት የሌላቸው አገራት ገዥዎች እንደ ቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ለብድርና ለእርዳታ የሚሄዱበት ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ሳይወዱ በግድ የዴሞክራሲ ጨዋታ ውስጥ እንዲገቡ ተገደዋል፡፡ የዓለማችን የደሃ አገራት አምባገነን መሪዎች የዴሞክራሲና የምርጫ ጨዋታ ውስጥ ሳይገቡ ከምዕራባውያን የሚያገኙት እርዳታ ቀጥ ሊል እንደሚችል ሰለሚውቁ ስለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሃሰት መዝሙራቸውን ለመዘመር ተገደዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢያደርጉ አምባገነናዊና በሙስና የተበከለ የገዥነት ታሪካቸው በቀላሉ በምርጫ ተሸንፈው ከሥልጣን እንዲነቀሉ የሚያደርጋቸው መሆኑን ይረዳሉ፡፡ ከእዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ውጤቱን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት፤ እነሱን ከሥልጣን መንቀል ቀርቶ ሥልጣናቸውን ሊገድብ እንኳን በማይችል መንገድ ውጤቱ አስቀድሞ የታወቀ የይስሙላ ምርጫ ማድረግ ከሁሉ የተሻላ አማራጭ አካሄድ ሆኖ አግኝተውታል፤ ዝርዝር አሠራሩንም ሰልጥነውበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ የማስመሰልና የማጭበርበሪያ ምርጫ የሚያደርጉ የዓለማችን አምባገነን ኃይሎች በርካታ ናቸው። ይህም ግንዛቤ የዓለማችንን የዲሞክራሲ ሂደት በአትኩሮት ከሚመለከቱት ታዛቢዎች አልፎ በአምባገነኖች ሥር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ የተረዱት ሃቅ ሆኗል፡፡ ይህ እውነታ ደግሞ አምባገነኖች ምርጫን እንዳሻቸው መቆጣጠር የሚችሉበት አቅማቸውና ብልጣብልጥነታቸው በሙሉ ተሟጦ ማለቅ መጀመሩን ያሳያል።

በይስሙላ ምርጫ የአገሩን ሕዝብና ዓለም-ዓቀፍ ማኅበረሰብን ማጭበርበር እንደማይችሉ የተረዱ አንዳንድ አምባገነኖች የማፈግፈግ እርምጃን ሲመርጡ (ለምሳሌ ኬንያና ዚምባብዌ) ሌሎቹ ግን ባገጠጠ መልኩ ሕዝብን የማፈንና የማስፈራራት እርምጃዎችንና ምርጫንም ከበፊቱ በባሰ በማጥበብ መሄድን መርጠዋል። (ለዚህ አይነቱ እብሪት የመለስ-በረከት አገዛዝ ሁነኛ ምሳሌ ሲሆን ግብፅና ምናልባትም ኢራን በሰሞኑ አካሄዳቸው ከቀጠሉ ተከታይ ምሳሌች ሊባሉ ይችላሉ)።

ወያኔ ምርጫን ምን ያህል በሙሉ ቁጥጥሩ ውስጥ እንዳስገባውና በማስመሰያነት እንደሚጠቀምበት ለመገንዘብ በ2000 ዓ.ም የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫዎች የተጫወተውን ቲያትር መመርመር በቂ ነው። በአዲስ አበባ ውስጥ ከሁለት ዓመታት በፊት አንድ ተመራጭ ማስመረጥ ያቃተው ወያኔ በዚህ ምርጫ ‹‹የከተማው አቸናፊ ተመራጮች ሙሉ በሙሉ የእኔ እጩዎች ናቸው›› አለ። ይህ በተዓምር ደረጃ ሊታይ የሚገባው ጉድ የሚያመለክተው የመለስ-በረከት ቡድን የሕዝብን ልብ የመቀየር ቀዶ ጥገና እውቀቱ እጅግ የረቀቀ፣ በዓለማችን ተሰምቶና ታይቶ ከማይታወቅ ደረጃ መድረሱን ነው። በተባባሰ ግድያ፣ እስራት፣ አፈናና ዘረፋ የሶስት አመት ግዜ፣ ወያኔ በአዲስ አባባ ውስጥ ከዜሮ ወንበር ወደ ሁሉንም ወንበር ባለቤትነት የተሸጋገረበት ሁኔታ የሚያረጋግጠው ያለ ዕውነተኛ የውድድር ቅድመ ሁኔታዎች ምርጫ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ነው፡፡

### 2.1 የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ?

ከላይ እንደጠቀስነው ከ20 ዓመታት የምርጫ ማጭበረበር ልምዶች በኋላ አምባገነኖች ለከተው በሰጡን መጠን ወንበር ተቀብለን ይህን ድርጊታችንን የዲሞክራሲ ሂደት ነው ብለን እርስ በርሳችን መከራከር የማንችልበት ህዝባችንንም ማጭበርበር ከማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በተለይ በ97 ምርጫ የድል ተራራ አፋፍ ላይ ደርሶ በወያኔ አጋዚ ጦር አሽቆልቁሎ እንዲመለስ የተደረገን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ወያኔ ሥልጣኑን ቅንጣት እንኳን በማትነካው መልኩ በሰጠን ወንበር ውስጥ ለመቀመጥ ብቻ ወያኔን በምርጫ ተብዬ ቀልድ ማጀብ የሕዝብ ወገኖች ለሆኑ ሁሉ በጭራሽ የማይመጥናቸው ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

የሕዝብን ስሜት የሚያስተጋቡ ተቃዋሚዎች ከአሁኑ ፈጥነው ማድረግ ያለባቸው ምርጫ ለአምባገነኖች የህጋዊነትነትና የሞራል ሽፋን መስጫ ሳይሆን እውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ ይህ ፍላጎት ብቻ የአገርን፣ የመንግሥትንና የዜጎችን እጣ የሚወሰን ልዕልና ያለው የሚሆንበትን ሁኔታ እንዴት እንፈጠራለን ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው፡፡ ባጭሩ እነመለስ በተጭበረበረ ምርጫ ዘረኛ፣ አምባገነናዊና የዘረፋ ስርአታቸውን የማስቀጠል ሥራ እየሰሩ መሆኑን በመረዳት መጪው ምርጫ በተጻራረው የሕዘብ ፍላጎት በነጻ የተገለጸበት ምርጫ እንዲሆን ለማድርግ አቅዶ መንቀሳቀስ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የቅንጅት መሪዎች እንዳደረጉት ድምጹን የተዘረፈውም ህዝብ ድጋፉን በደሙ ሳይቀር እንደሰጠበት፣ ምርጫ የአምባገነንነት መጋረጃ ሳይሆን በእውነት ለመንግሥት ሥልጣን መወዳደሪያ እንዲሆን የሚያስፈልጉትን አገራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ፣ ለእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የኢትዮጵያን ሕዝብና የወያኔ አፈና አላነቃንቅ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ በማስተባበር መታገል ነው፡፡ ይህን ትግል በውጭ በሚገኘውና ትልቅ አስዋጽኦ ማደረግ ወደሚችለው ኢትዮጵያዊም ማድረስ ይገባል፡፡ ሃቀኛ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በአገርችንና በአካባቢያችን ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ይነካል ብለው ለሚያስቡ የዲፕሎማሲያዊ ማኅበረሰባትና ለራሱም ለወያኔ ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህ በኩል እስካሁን መኢአድ ያደረገው በአርአያነቱ የሚጠቀስ ነው።

**ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል**

በደብዳቤና በኢሜል ከደረሱን በርካታ የህዝብ አስተያየቶች ውስጥ የሚከተለው ድብዳቤ የአዘጋጆችን ቀልብ ስለሳበ ለናንተ ለአንባቢያን አቅርበናል። የመልዕክቱ ባለቤት በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ዘረኝነት ተማረው በስደት ላይ ይገኛሉ።

## ይድረስ ለአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት በሙሉ

ቺፍ እንስፔክተር ካሳሁን ብርሃኑ
የቀድሞ የአዲስ አበባ ፖሊስ ባልደረባ

ይህንን አጭር መልእክት እንድፅፍ ያነሣሣኝ ነገር ቢኖር ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ መንግሥት ላለፉት 18 ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውና አሁንም በማድረስ ላይ ያለውን ግድያ እስራት እንግልት ሥቃይ ግፍና እና መከራ አልበቃ ብሎት በቀጣይም ይህንኑ የአፈናና ሕዝብን እረግጦ የመግዛት ፖሊሲውን ለማሳካት ደፋ ቀና በማለት ላይ እንደሚገኝ ለእናንተ የተሠወረ አይደለም። እስቲ የቅርቡን የ1997 ዓ ም ሁኔታ እናስበው ስንት ወገኖቻችን የጥይት ሠለባ ሆኑ? ስንቷ ድሀ እናት ልጄ ነገ ተምሮ ይጦረኛል ስትል በራፏ ላይ በጥይት ወድቆ ቀረ? የአባሎቻችን ወንድሞች ለዚያውም ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሁለት ሰዎች አልተሰውም? የአቃቂ ክ/ከተማ ትራፊክ ፖሊስ አባል በምሽት በሥራ ላይ በነበረበት ቦታ ንፋስልክ አካባቢ ከደህንነቶች መኪና ውስጥ በተተኮሰ ጥይት ሰኔ 4/97 ምሽት ተመቶ አፋጣኝ እርዳታ ሣይደረግለት ልጆቹን በትኖ ህይወቱ ማለፉንና በወቅቱ የነበረው የ7ቱ ኮማንድ ፖስት ሀለፊ በስህተት በእኛ ሰዎች ነው የተመታው ብሎ መናገሩንና በማግስቱ ጉዳዩ ተድበስብሶ መቅረቱን በዕለቱ ተረኛ አዳሪ የነበራችሁ የክፍለ ከተሞችና የኮሚሽኑ ጽ/ቤት መረጃ ሠራተኞች አታውቁም? ሰኔ1/97 እናቴ አድኑኝ ብሎ በ60 ዓመት ባልቴት አግር ሥር ተጠምጥሞ ተማፅኖ የጠየቀ ታዳጊ ወጣት ባልቴቷን ጨምሮ ሁለቱም በአንድ ጊዜ በጥይት ተመተው የተሠዉትን እንረሳለን? በመኖሪያ ሰፈራቸው ውስጥ በአጋዚ ጦር አልሞ ተኳሾች ግምባራቸው እየተመቱ የወደቁ ወንድሞቻችን አስከሬን ሥርዓት በጎደለው ሁኔታ የሟቾች ቁጥር እንዳይታወቅ በሚል ከተለያዩ ሆስፒታሎች እተሠበሠበ ጦር ሀይሎችና ፖሊስ ሆስፒታሎች እንዲገባ የተደረገው በእኛው አለቆች ትዕዛዝ አልነበረም? አስከሬን ለመረከብ እንኳን ባንክ ሊዘርፍ ሲል ነው የተገደለው ብለው እንዲፈርሙ ወላጆች አልተደረገም የችግሩ ተጋሪ አይደለንም?

የንፁህን ዜጎቸ ደም በፈሠሠበት የተቀረውንም ህዝብ በማጎሪያ ማዕከላት ባስገቡበት ምሽት የውጭ ጠላት ድል የነሱ ይመስል በንፁሀን ደም የተሞላ መለኪያቸውን በማንሳት ዳንኪራ ሲረግጡ የነበረውን ምንጊዜም ቢሆን የማንረሳው ዕውነታ ነው። በእኩለ ሌሊት ከየመኖሪያ ቤቱ ታፍሶ ወደ ዲዴሳ ወታደራዊ ካምፕ እንዲጋዝ ከተደረገው ህዝብ ምን ያህሉ እንደከብት በጭነት መኪና ተጠቅጥቆ ሲጋዝ በደረሠበት እንግልት ህይወቱ አለፈ? ስንቱስ በቂ ህክምና ሣያገኝ በካምፕ ውስጥ ለእልፈተ ህይወት በቃ? በወቅቱ እንኳን አስክሬናቸውን ወዴት እንደሚወስዱት እንዳናይ እዚያ አካባቢ እንዳንደርስ ተከለከልን የምትሉ አባላት አልነበራችሁም? ስንቱስ ነው ለአእምሮና ለአካል ጉዳት የተዳረገው፤ ከአዲስ አበባ በፍርድ ቤት በዋስ ተለቀው ከነመፈቻ ወረቀቶቻቸው ወደ ዝዋይ እና ዲዴሳ ማዕከላት ተወስደው የተጣሉት ዜጎቻችን ቁጥር ምን ያህል ነው? ከዝዋይና ከዲዴሳ ማዕከላት ከተለቀቁ በኋላ ለሆዳቸው ባደሩ የመስተዳድር አካላት እየተመረጡ እነዚህ እረብሻ የነበረበት ሠፈር ልጆች ናቸው እየተባሉ በድጋሚ በሄዱበት መኪና እንዲመለሱ ተደርገው ለእስራትና እንግልት የተዳረጉት ምን ያህል አንደነበሩ በወቅቱ በሥፍራው የነበርን የምናውቀው ነው፡፡

ወያኔ በምርጫ 97 ወቅት በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የፌደራል ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት አባላት በተለያዩ ካምፖች እየዞሩ 2 እና ከዚያ በላይ የምርጫ ካርድ እንዲወስዱ መደረጉንና እነርሱ ግን በተቃራኒው ምን ያህል ለቅንጅት ውጤት ማድመቂያ እንደሆኑ አይተናል። በምርጫው ማግስት ቅንጅት አዲስ አበባን ይረከብብኛል በሚል ሥጋት አስቸኳይ ትዕዛዝ ለአዲስ አበባ ቤቶች ኤጀንሲ ጽ/ቤት በመሥጠት በፌድራል ፖሊስ በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ የራሱ ብሔር አባላት ለእያንዳንዳቸው በነብስ ወከፍ ኮንደሚየም ቤትና 105 ካ.ሜ መሬት በተለያያዩ ቦታዎቸ በተለይ በንፋስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማና ቃሊቲ አካባቢዎቸ በነፃ እንዲታደላቸው መደረጉን አብዛኞቻችን የምናውቀው ሀቅ ነው፡፡ ይህም የተሸከምነው አምባገነን ምን ያህል ዘረኛ መሆኑን ያሣያል። ከዚሁ ምርጫ ጋር ተያይዞ በሺዎች የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት ለዘረኞች አንተባበርም በማለት ሥራቸውን በፍቃዳቸው ለቀዋል። ብዛት ቁጥር ያላቸው አባላት ከፖሊሳዊ ሙያ ሥነ ምግባርና ህግ ውጪ የአላፊ ትዕዛዝ አልፈፀማችሁም በሚል ከሥራቸው ተባረዋል። በመደበኛው ፖሊስ ማሰልጠኛ እና በኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ በምረቃ ወቅት ባንዲራ ላይ ተደፍተን « ህዝብን ከማንኛውም አደሎአዊ አሠራር በነፃ በታማኝነት እና በቅንነት ለማገልገል ቃል እንገባለን » ብለን ነበር፡፡ በእርግጥ አሁን በህጉ መሠረት ነው የምንሠራው?

ወያኔ ከዚህ ቀደም በህዝብ ላይ የሠራው ግፍ አልበቃ ብሎት እነሆ ዛሬም ምርጫ በሚለው የቅጥፈት ወሬው የህዝብ አመፅ ቢነሣብኝ በሚል ሥጋት ሁል ጊዜ የሚመካበትን በመሣሪያ የአፈና መዋቅሩን የበለጠ ለማስፋፋት እላይ እታች በማለት ላይ ይገኛል። በቅርቡም ለዚሁ እኩይ አላማው ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ከዚህ ቀደም እንደሚያደርገው በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል በሠራዊቱ አባላት መካከል ልዩነት መፍጠር አንዱን ታማኝ ሌላውን አፈንጋጭ በማለት፣ ታማኝ ለሚላቸው እንደ የብሔራቸው የአማራ ልማት ማህበር፤ የኦሮሞ ልማት ማህበር፤ የደቡብ ልማት ማህበር እና የመሳሰሉት አባላት በሚል ቅጥያ በማበጀት፣ የራሱ የፖለቲካ ድርጅት አባላት በማድረግ ሌላውን የሠራዊቱን አባላት እረግጠው እንዲይዙለት እንዳደራጀ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው፡፡ የስልጣን ዕድሜዬን ያራዝምልኛል ብሎ ላወጣው ህግ እንኳን የማይገዛ አረመኔን እስከመቼ እንሸከማለን? ህጉ “ማንኛውም የሠራዊት አባል በሥራ ላይ እያለ የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን አይችልም” ይላል፣ ይሁን እንጂ ወያኔ ህጉን ለራሱ እንዳሻው የሚጠቀምበት መሆኑ ከማናችንከማናችንም የተሠወረ አይደለም፡፡ ወያኔ የፈለገውን ቢሆን፣ የእኔ ታማኝ ነው ብሎ በህላፊነት ለይስሙላ ቢያስቀምጥህም፣ ውሣኔ ሰጪው ግን ከአንተ ሥር ያለው የወያኔ ብሔር አባል መሆኑን ታውቃለህ።

እኛ በዘረኞች ተረግጠን የራሣችን ወገን በእኛው ሲረገጥ ህሊናችን ይቀበለዋል? የእናቶቻችን ዋይታና ለቅሶ ለአፍታ እንኳን አይታየንም? የሰው ልጅ በየመንገዱ በጠራራ ፀሐይ እየወደቀ የወላጆች ለቅሶና ዋይታን መመልከት ከዚያም በላይ እምባውን ከሚያፈሰው ህብረተሠብ ጎሮሮው ተነጥቆ እየተሠበሠበ የሚሠጥ ደሞዝ እየተቀበሉ አሜን ብሎ መኖር ይቻላል? አንዳንዱ ህሊናውን ሸጦ መኖር ይችል ይሆናል ነገር ግን ለዘላለም የማይጠፋ ጠባሣ ለዘር ትቶ ማለፍ የባሰ ሞት ይመስለኛል። እራሣችንን ነፃ ካላወጣን ማን መጥቶ ነፃ እንዲያወጣን እንፈልጋለን? ምንም ማድረግ ባንችል እንኳን የከፉዎች አገልጋይ ከመሆን ራስን ማውጣት ትንሽም ቢሆን የአእምሮ እረፍት ይሠጣል፡፡ ትግል ከራስ ይጀምራል። በእኔ እምነት የትግል ትንሽ የለውም። በህዝብ ላይ በሚፈፀመው ግፍና አድሎ ካለመተባበር ጀምሮ የሚሠራውንም ማጋለጥ በራሱ አንድ ትግል ነው። ሁላችንም ነግ በእኔ የሚለውን ማሠብ ይኖርብናል። እኔ ምንቸገረኝ የሚለውን ትተን በጋራ ካልተነሣን ዛሬ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው መከራ ነገ ወደ እኛ መምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

**የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቅርብ ነው!!!**
**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ሞት ለዘረኛው የወያኔ ሥርዓት**

## ወያኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የማህበረ ቅዱሳን አባላት የህን በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ ሙስና ለማጋለጥ የወሰዱት እርምጃ የሚደነቅ መሆኑን ያነጋገርናቸው ስዎች ገልጻው ህብረተሰቡም ጉዳዩ የሀይማኖት ሳይሆን አገርን ከዘራፊዎችና ከዘረኞች የማዳን ተግባር በመሆኑ ድጋፉን ሊሰጣቸው ይገባል ተብሏል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ አገራችንን ከውጭ ወራሪዎች ለመታደግ ያደረገችውን ጥረት ያስታወሱት አንድ ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉ አባት፤ አሁን በማህበረ ቅዱሳን በኩል እየታየ ያለው አገርን የማዳን ዘመጃ ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባል ብለዋል። እኝህ አባት እንደገለጹት አባ ጳውሎስ ማህበረ ቅዱሳኑን በፖለቲካ ወስጥ ጣልቃ እየገቡ ነው የሚል ክስ ማቅረባቸው በተለይም ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ ተደጋግሞ የሚሰማ ጉዳይ ነው ካሉ በሁዋላ፣ እውነታው ግን ወጣቶቹ አገራቸውን ከመፈራረስ ለመታደግ እረሳቸውን መስዋት እያደረጉና የአባቶቻቸውን አደራ እየተወጡ ነው እንጅ ስልጣን ለመያዝ እያለሙ አይደለም” ብለዋል።

በ1997 አም ተፈራ ዋልዋ በአዋሳ ከተማ ለተሰበሰቡ የወያኔ ካድሬዎች “ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ የነፍጠኞች መሸሸጊያ ምሽግ ሆናለች” ማለቱ ይታወሳል።

ግንቦት 7 ወያኔ በሀይማኖት ተቃማት ላይ የሚወስደውን ተደጋጋሚ ጥቃት ሲያወግዝ መቆየቱ ይታወሳል።

የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ለአዲስ አመት ባስተላለፉት መልእክት ላይ ወያኔ “ማህበረሰቡ በጽኑ የሚያምንባቸውን ከዚህ ጊዜያዊ አለም ይልቅ ለማያልፈው ዘላለማዊ ሕይወት ቆመናል የሚሉ የሀይማኖት ተቁዋማትንና የሀይማኖት አባቶችን፤ ከማንም ተራ ሰው ያልተሻሉ፤ ለስጋቸው ያደሩ፤ የነዋይ ፍቅር ያሰከራቸው ሰዎች እስከሚመስሉ ድረስ እርስ በእርሳቸው ያባላቻዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ባደባባይ በተራ ዱርዬዎች ጳጳሳት ሲደበደቡና በራቸው ሲሰበር ህዝቡ እያየና እየሰማ፤ እግዚአ የሚባልበት ቦታ እንኩዋን እንደሌለ እንዲያምን፤ ሞራሉ ጭራሹኑ እንዲላሽቅ ያደርገዋል፡፡ ይህ አልበቃ ብሎት አብረውና ተከባብረው የኖሩ ሀይማኖቶች እንዲጋጩ፤ በደሴ ላይ እንዳደረገው አንደኛው ሀይማኖት የአንደኛው ምቀኛ፤ ለአንዱ የተባለውን መሬት ሌላው ተቃውሞ እንዳስከለከለ አድርጎ በቡችሎቹ በማስወራት፡ አልጋጭ ሲሉለት የሚያጣላበት ሌላ ዘዴ ሲያሰላስል ያድራል” ማለታቸው ይታወሳል፡፡

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org